## *ብዙ አየሁ የሕይወቴ ታሪክና ትዝታ*

በአቶ ታደሰ ገብረኪዳን ተደርሶ በዘጠኝ ምዕራፍ የተከፈለ ባለ 559 ገጽ የሕይወት ታሪክ
(ሻማ ቡክስ፥ አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም. ISBN 99944-0-002-9)

**ጌታቸው ኃይሌ**

ጸሐፊው ክቡር አምባሳደር ታደሰ ገብረኪዳን ሙህር (ጉራጌ) ውስጥ ታችኛው የሳንቃ ኅዳር 5 ቀን 1938 ዓ.ም. ተወልዶ እስከ 1945 ዓ.ም ድረስ የኅብረተሰቡን ባህል እየወረሰ ጎልምሷል። ከተወለደ ጀምሮ መጽሐፉን ኦታዋ (ካናዳ) ሆኖ ጽፎ እስከጨረሰበት ዘመን ድረስ እውነትም ብዙ አይቷል። ሙህር ውስጥ ያለው የሕፃናትና የሽማግሌዎች ሕይወት መላልሶ ቢያነቡት አይጠገብም። ታሪኩን የሚያነብ ሳያስበው እንደኔ ወደራሱ አስተዳደግ ይሄድና ሁለቱን አስተዳደጎች ያስተያያል። በአማራና በጉራጌ ማህል (እኔ እንደማውቀው በኦሮሞ ባህል ውስጥም) ያለው የባህል ተመሳሳይነት ቋንቋ ባህልን እንደማይከለክለው ያሳያል።

ታሪኩን የጻፈበትን ምክንያትና በመጻፉ የተሰማውን ደስታ ሳነብ የየራሳችንን ታሪክ ተመካክረን የጻፍነው መሰለኝ። ስለአባቱ ስለ አቶ (ጋኀ) ገብረኪዳን/ስራግ/ስራጋ አትጋቦና ስለራሱ ልጆች አስተዳደግ የጻፈው ስለ አባቴና ስለልጆቼ ከጻፍኩት ጋር ይመሳሰላል። ሊጽፍ የተነሣው የግል ትዝታውን ስለሆነ ሁኔታው አስገድዶት ነው እንጂ፥ ስለአባቱ የጻፈው ምጥን ባይሆን የቱን ያህል በወደድኩ! ቃላቸው እውነትም ሰው እንደሚለው ከመሬት ጠብ አትልም፤ እንደሳቸውና እንደ "አባባ አሶሬ" (ገጽ 27) ያሉ አባቶች የኅብረተሰቡ ሕይወትና መድኃኒት ብቻ ሳይሆኑ ለሚቀጥለው ትውልድ የጨዋነት ባህል አውራሾች ናቸው። እንደዚህ ያሉ አባቶች አርአያነታቸውን ለዘመኑ በጎ ገጽታ እንዲስማማ ያህል በጥቂቱ ካስተካከሉ በኋላ በብዛት እንዲያጥለቀልቁን እመኛለሁ። ስለማስተካከሉ ምን ማለቴ እንደሆነ በኋላ በአንድ ጥቅስ እገልጻለሁ።

የ*ብዙ አየሁ*ን ትልቁን ክፍል የያዘው፥ የደርግ ዘመን ነው። ደርግ ግዛቱን ሲጀምር ጀምሮ እስከመጨረሻው አገልግሏል፤ ታማኝነቱ የኢ.ሠ.ፓ.ኮ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልነትን አትርፎለት ተቀናቃኞቹ ሊያመጡበት ከሚችል አደጋ ድኗል። በዚያ ዘመን አቶ ታደሰ የአዲስ አበባ ባንክ አዛዥ፥ የውጭ ንግድ ሚኒስትር፥ በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖና በልዩ ልዩ የቦርድ ስብሰባዎች አባልነት ሀገሩን በታማኝነትና ከስሕተት የሚያርቅ ጥንቃቄ አድርጎ አገልግሏል። ሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ የነበረበት ዋናውና ታላቁ ፈተና ሰዎች የንግድ ፈቃድና የውጪ ምንዛሪ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉበት ተጽዕኖ ነበር። ከአማላጆቹ ውስጥ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አባትና ወንድም ይገኙበታል። እሱ ግን አልተሸነፈላቸውም፤ አንድ ጊዜማ ሳያነጋግራቸው ከቢሮው በራፍ እንዲመለሱ አድርጓል።

በአቶ ታደሰ ግምት፥ እነዚህ ሁለት ሰዎች ሻለቃ መንግሥቱ (በጸሐፊው አነጋገር "መንጌ") ሳይሰማ በየመሥሪያ ቤቱ እየዞሩ ተመሳሳይ ችግር ሳይፈጥሩ አይቀሩም። ብዙዎች እንደተሸነፉላቸው ባይነግረንም መገመት አያዳግትም። እነሱ ብቻ ሳይሆኑ፥ ከደርግ ባለሥልጣኖችም አንዳንዶቹ "እገሌ ሊያነጋግርህ ይመጣልና ተቀብለህ አነጋግረው" እያሉ እንደሚያስቸግሩት ሳይደብቅ ጽፎልናል። አቶ ታደሰ "አየሁ" ብሎ የጻፈውን ታሪክ እንዳምን ያደረገኝ ስማቸውን ከሚጠራቸው ሰዎች ብዙዎቹ አሁንም በሕይወት ስላሉ፥ ቢሳሳት መልስ ሊሰጡ እንደሚችሉ ሳያስብበት አይጽፍም የሚለው ግምቴ ነው። ሁለተኛም በወጣትነቱ አንጥረኛ ዘመዶቹ ምርታቸው የጥንት እቃ የሚፈልጉ አገር ጎብኝዎችን ለመደለል ያደርጉት የነበረውን ማጭበርበር ሳይደብቅ መናገሩ ለእውነተኛነቱ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

ስለደርግ ዘመን ሲጽፍ ከባንኩና ከንግዱ ዓለም ወጣ እያለ የታዘበውን በሰፊው ሊጽፍ ያልፈለገው ሊጽፈው የሚችለው ነገር ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን፥ ለመጻፍ ስላልፈለገ

ይመስለኛል። ግን የሰው አእምሮ በቃኝ አይልም እንጂ፥ ብዙ ጽፎልናል። በትዝታዬ ከሚቀሩት አንዳንዶቹን እየመረጥኩ እጠቅሳቸዋለሁ።

> አንድ ጊዜ የመንግሥት የቡና ምርት መንግሥቱ የተማመነበት ሆኖ ሳለ፥ ግብርናው ለምን እንዳልሠመረ የቡናና ሻይ ልማት ሚኒስትር ቢጠየቅ "ጥፋቱ የኛ ሳይሆን የባንክ ነው፤ የጠየቅነውን ገንዘብ ብድር በወቅቱ አይሰጡንም፥ . . . የተደራረቡ ጥያቄዎች እያቀረቡ አስቸገሩን መሥራት አልተቻለም" ይላል። መንግሥቱ አቶ ታደሰን "በቁጣ ቃል፥ ተነስና አስረዳ" ይለዋል። አቶ ታደሰ፥ "(ብድር ጠያቂዎቹ) ያቀረቡት የብድር ጥያቄ የባንክን የብድር መለኪያዎች ስለማያሟላ ብድር መስጠቱን አላመንበትም" የሚል መልስ ይሰጣል። በዚህ ጊዜ "አጅሬ ማን አለብኝ" በወላፈን መላሱ፥ "ያንተን እምነት ማን ጠየቀህ? ያንተ እምነት እዚህ ቦታ የለውም፤ አብዮታችንን የሚፈታተኑትን እንፋረዳቸዋለን" ብሎ የስብሰባውን አዳራሽ ረግጦ ወጣ (ገጽ 306-7)።

ግን አልተፋረደውም፤ እንዴት በሥልጣን ላይ አቆየው? ለሀገሩ ያለውን ታማኝነት አይቶለት ከሆነ፥ መንግሥቱን በድንቁርናውና በጨካኝነቱ ብቻ እንፈርድበታለን እንጂ፥ ለኢትዮጵያ እድገት ማሰቡን አንጠራጠርም። ጸሐፊው እንደሚለው፥ "ኤኮኖሚው በይበልጥ እንዳይዳከምና ለጦሩ ክፍል ተፈላጊው ገንዘብና ቁሳቁስ እንዲቀርብለት በየስፍራው የነበሩ ሲቪል ቴክኖክራቶች ጠንክረው ባይዙ ኖሮ የደርግ እድሜ ያጥር እንደነበር ጥርጥር የለውም" (ገጽ 267)። አምባሳደር ታደሰ ስለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጠባይ ማንነት የጻፈው የኢትዮጵያን ታሪክና የሳይኪያትሪ ተመራማሪዎች የሚፈልጉት ነው።

ለማንኛውም፥ እንዲህ ያለ አነጋገር መንግሥቱ ብቻ ሳይሆን፥ ራሱ ብዙ ተረቶች የሚነግረን ታደሰም ቀጥሎ ያለውን ጽፎልናል፤ "ገሰሰ ወልደኪዳን የብሔራዊ ኤኮኖሚ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ አንድ ቀን ይጠራኝና ቢሮው እሄዳለሁ። ስማ ታደሰ፥ አንድ የኦሮምኛ ተረት ልንገርህ ይለኛል። እንቁራሪቶቹ እንዳይሞቱ ኩሬውም እንዳይደርቅ ይባላል አለኝ። . . . በወቅቱ የነበረኝ ተግባራዊ ምላሽ፥ ለተረት ጊዜ የለኝም፤ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ እየተጣደፍኩ ነኝ የሚል ነበር" (ገጽ 256-7)።

ትውልዱ ከጉራጌ የሆነ የአቶ ታደሰን አስተዳደግ የሚያነብ ኢትዮጵያውያን በጎሳ እንደማይከፋፈሉ በግልጽ ያያል። ለምሳሌ፥ እንዲህ ሲል ይጽፋል፤ "የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ስብጥር ሚዛናዊ ነበር ማለት ይቻላል። ጓደኞቼ የምንመራረጠው ብሔረሰብን መሠረት አድርገን ሳይሆን የአስተሳሰብና የዝንባሌ መሰሎቻችንን እየፈለግን ነበር። የኔ የቅርብ ጓደኞች ያኔም እንዳሁኑ ከልዩ ልዩ ብሔረሰቦች የሚመጡ ናቸው። ሰውን በሰውነቱ እንጂ በጎሳው ምክንያት መጥላት ወይም መውደድ፥ ማንሳት ወይም መጣል እኔን የተጸናወተኝ በሽታ አይደለም" (ገጽ 63)። ጨቋኝ ገዢዎች ጉራጌዎችን በጎሳ ስማቸው ጠርተው ሲንቋቸው ሲያይ፥ "አማሮች ጉራጌዎችን ናቁ" አላለም (ገጽ 352)። ወደአማራው ዘንድ ሲመጡ፥ ሽማኔ፥ ፋቂ፥ ሸክላ ሠሪ፥ ኮርቻ ሰፊ የሚል ስድብ እንደሚያመጡ ያውቃል።

ከዚሁ ጥያቄ ጋር የተያያዘውን ወያኔዎች ያመጡብን በጎሳ የመከፋፈል ፖሊሲ አደገኛነት ለማሳየት ታደሰ ከዚህ በታች ያለውን የጉራጌ ንጉሦች ታሪክ በምሳሌነት ያስተምረናል፤

> አንድ (የጉራጌ) ንጉሥ የጎሳው የበላይ ዳኛ፥ አስታራቂ፥ አስተባባሪና ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች ዋና ተወካይና ሲያስፈልግም የጦር መሪ ነበር። መገመት እንደሚቻለው የማእከላዊው መንግሥት ሥልጣንና ኀይል በጉራጌ መሬቶች ላይ እየተጠናከረ ሲመጣ የጎሳዎች ንጉሦች ሥልጣን እየቀነሰ ሄደ። በአሁኑ ወቅት የማንገፍር ንጉሥ ዙፋን ክፍት ነው፤ በቅርቡ ይሞላል ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን ሕዝብን በጎሳ የመሸንሸኑ ተግባር ከተገፋበትና ስር እየሰደደ ከሄደ የጎሳ ንጉሥነት በአንድ ቅርጽ ወይም በሌላ ተመልሶ ሊመጣ ይችላል። ማእከላዊው መንግሥት ከመጠናከሩ በፊት የነበረው ዓይነት በጎጥ ተከፋፍሎ መጋጨትና መዋጋት የነገው ዕጣችን ሊሆን ይችላል (ገጽ 23)።

በአሁኑ ጊዜ የዓለምን ኢኮኖሚ ያቃወሱ ስግብግቦች ኢትዮጵያ ውስጥም ቀደም ብለው በቅለው ስለነበረ፥ የዓለም ኢኮኖሚስቶች ነገር ሳይበላሽ ቀደም ብለው ከኢትዮጵያ ሊማሩ ይችሉ ነበር፡፡ አቶ ታደሰ ታሪኩን እንዲህ ሲል አሣምሮ አቅርቦልናል፤

> አንድ ቀን የዋናው ቦርድ ኮሚቴ አባላት አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘውን የኮታሪና የበለጠ ሺበሺ የቡና ላኪ ድርጅቶችን . . . ተዘዋውረን ጎበኘን፡፡ ኮታሪ ከፍተኛ የብድር ተጠቃሚ ነው፡፡ . . . የጉብኝቱ ዕለት የቡናው መጋዘን ጢቅ ብሎ ሞልቷል፡፡ እዚህ ምን ያህል ቡና አለ? ብለን ጠየቅነው፡፡ መልሱን ነገረን፡፡ ጥቂት ጆንያዎች መዝነው አሳዩን፡፡ ቁጥሮች አባዝተን ከደማመርን በኋላ፥ "ዓለም ጤና ናት፥ እዳስቀመጥናት አገኘናት፥ የሰጠነው ብድር አልባከነም" . . . ብለን ተነስተን ልንወጣ ስንል፥ ከቁመቱ ማጠር የተነሳ መኪና ሲነዳ የኋላ ማርሽ አይሆነኝም እያለ በራሱ ላይ የሚቀልደው የባንኩ ሦስተኛው ሰው አቶ ገብረ መድህን፥ "እስቲ ክብደቴ ስንት እንደሆነ ልወቅ" ይልና በቡናው ሚዛን ላይ ተነስቶ ይቆማል፡፡ ቁጥሩን ትክ ብሎ ያየዋል፡፡ አቶ ሚዛን ገብሬን፥ "ትናንት ከነበርክበት የክብደት ደረጃ በአንድ ቀን በ30 ኪሎ ጨምረሃል እንኳን ደስ ያለህ" ይለዋል፡፡ . . . የሌለ ቡና አለ እየተባለ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የባንኩ ገንዘብ እንደተጭበረበረ ግልጽ ሆነ፡፡ ባንኩ ለብዙ አመታት ገንዘቡን ለማስመለስ ያልተቆጠበ ጥረት ቢያደርግም አብዛኛውን መሰብሰብ ሳይቻል ቀረ (ገጽ 110)፡፡

አቶ ታደሰ ከውጭ አገር ለሚገኝ የገንዘብ እርዳታ በስምምነቱ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ መፈረም ያለበት ባለ ሥልጣን ስለነበረ፥ በዚያ ሂደትም "ብዙ አየሁ" ሊል ይችላል፤ የኢትዮጵያን መብትና ክብርም አስጠብቋል፡፡ ለምሳሌ የሊቢያው ፕሬዚዴንት ሙአመር ቀዛፊ ስለረዳው የ150 ሚሊየን ዶላር የአፈራረሙ ስነሥርዓት ላይ የነበረው ታሪክ የጸሐፊውን አኩሪነት ከማሳየቱ በላይ የችግሩና የመፍትሔው ታሪክ ሊነበብ የሚገባው ድራማ ነው፡፡ በአጭሩ ልጥቀስለት፤

> ችግሩ የተፈጠረው (በአረብኛና በእንግሊዝኛ ተጽፈው የቀረቡት) ሁለቱ ስምምነቶች በትርጉም ባይስማሙ የበላይነት የሚኖረው የትኛው ነው? በሚለው ላይ ነበር፡፡ እኛ "ዓለም በተቀበለው አሠራር ሁለቱም እኩል ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል" ስንል በነሱ በኩል ደግሞ "አረብኛው የበላይነት ይኖረዋል ብለህ ካልተስማማህ ስምምነቱን በምንም ዓይነት (አ)ንፈራረም(ም)" ብለው ድርቅ አሉ፡፡ "የማንሠራበት ቋንቋ እንዴት የበላይነት ይኖረዋል ብለን እንድንፈርም እንጠየቃለን? በአረብኛው የስምምነት ረቂቅ ውስጥ ምን እንደተጻፈ እንኳን አናውቅም" ብዬ ተከራከርኩ፡፡ "በምንም ዓይነት ሐሳባችንን አንለውጥም፤ ካልፈለግህ ትተኸው ወደ አገርህ መመለስ ትችላለህ፤ ሁሉም ገንዘብ ፈላጊ የአፍሪቃ አገር የሚፈራረመው አረብኛው የበላይነት አለው እያለ ነው" . . . ብለው ሊያሳምኑኝ ወይም ሊያግባቡኝ ሞከሩ፡፡
>
> ውሉን ለመፈራረም እንዳልተቻለ (ምክንያቱን) ገልጬ መልዕክት (ወደ) አዲስ አበባ አስተላለፍኩ፡፡ . . . ዘግይቶ የመጣልኝ መልስ የሚለው፥ "እምቢ ካሉ ምንም ማድረግ አይቻልም፥ ከእነሱ የሚጠበቀው ገንዘብ በጣም ብዙ ስለሆነ ባሉት መሠረት ውሉን ተፈራርመህ እንድትመጣ" የሚል ነበር፡፡ "የመጣ ይምጣ እንጂ በምንም ዓይነት አረብኛው የበላይነት አለው ብዬ አልፈራረም" . . . አልኩና ሻንጣዬን ቀርቅቤ ከትሪፖሊ ለመውጣት ተነሳሁ፡፡
>
> የሆቴል ሒሳብ ለመክፈል ገንዘብ ያዥው ዘንድ ሄደን ሒሳቡን እንዲሠራልን ጠየቅነው፡፡ . . . "ሒሳቡ ተከፍሏል" ተባልን፡፡ . . . "የሊብያ ማእከላዊ ባንክ እንግዶቼ ናቸው እከፍላለሁ ብሏል" አሉን፡፡ በልባችን "ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ካንቋሸሸን ባንክ በምንም ዓይነት ግብዣ አንቀበልም" አልንና፥ "እግዜር ይስጥልን፥ እራሳችን እንከፍላለንና ሒሳቡን ሥሩልን" ብለን ደጋግመን ጠየቅን፡፡ . . . ግማሽ ሰዓት ያህል ከተጨቃጨቅን በኋላ ሒሳቡ ተሠራና ከፍለን ወደ አየር ማረፊያ ነጎድን፡፡
>
> ግማሽ መንገድ ያህል እንደተጓዝን የትራፊክ ፖሊስ ተሽከርካሪዎች በማስጠንቀቂያ መብራት አስቆሙን፡፡ ሾፌሩ "ምን አጥፍቼ ነው?" ቢላቸው፥ "የምንፈልገው አንተን

ሳይሆን እንግዶቹን ነው፤ ያስቀምናችሁ የሊብያ ባንክ የላከላችሁን መልዕክት ልንነግራችሁ ነው፤ ውሉን ለመፈራረም ተዘጋጅተናልና ተመልሳችሁ እንድትመጡ ብለዋል" ተብሎ ተነገረን፡፡ . . . ምንም ደሃ ብንሆን ክብራችንን አልሸጥንም አልኩ፡፡

(ከ)ባንኩ እንደደረስን ምክትል አዛዡ(ን) ሲያደርቁን ከሰነበቱት ተደራዳሪዎች ጋር ተቀምጦ አገኘነው፡፡ ገና ከመቀመጤ "ሐሳብህን ለውጠህ እኛ ባልነው መሠረት ልትፈራረም ተመለስካ?" ይለኛል፡፡ ብልጭ አለብኝና ተነሥቼ ቆምኩ፡፡ ወደበሩ አመራሁ፡፡ ሰውየው እንደማልበገር ሲያይ፥ "እኔስ ቀልዴን ነበር" አለና እንድቀመጥ ጋበዘኝ፡፡

"ሰነዱ ባልከው መሠረት ተስተካክሎ ተጽፏል፤ አሁን ከሁለታችን የሚጠበቀው መፈረም ብቻ ነው" ካለ በኋላ፥ በእንግሊዝኛና በአረብኛ የተዘጋጁትን ሰነዶች ከዴስኩ መሳቢያ አውጥቶ መፈረም ጀመረ፡፡ "ከመፈረሜ በፊት እንግሊዝኛውን ማንበብ አለብኝ" እለዋለሁ፡፡ "ምነው አታምነኝም እንዴ?" ይለኛል፡፡ ተስተካክሏል ያለው አንቀጽ ሳይስተካከል እነሱ በፈለጉት ዓይነት የተጻፈው ሆኖ አገኘሁት፡፡ በፍጹም ማመን አቃተኝ፡፡ . . . ይሄኔ በእርግጥም በጣም አምርሬ ቦርሳዬን አንጠልጥዬ ተነሳሁ፡፡ ግንኙነታችን (ከ)መጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱን ሰውዬው ስለተገነዘበና ካሁን በኋላ በማባበልም ሆነ በማታለል ሊመል(ሰኝ) እንደማይችል ስላወቀ፥ "አንተ የማትቻል ሰው ነህ፤ ይልቅስ ናና ተቀመጥ፤ እንፈራለም" ብሎ የተስተካከለውን ጽሑፍ ከሌላ የጠረጴዛ ኪስ አውጥቶ እንድፈርም ሰጠኝ (ገጽ 239-41)፡፡

ከዩጎዝላቮች ጋር የነበረው ውልማ ውጫሌን የሚያስታውስ ነበር፡፡ ታሪኩን የሚያውቀው አቶ ታደሰ፥ እግረመንገዱን ታሪክ የማወቅን አስፈላጊነት ለማስረዳት በልቡ እንዲህ ሲል አስቦ እንዲያስተካክሉ አስገደዳቸው፤ "ከውጫሌ ውል ጋር ተመሳሳይነት ነበረው፤ ጣሊያኖች ከሌላው ዓለም ጋር የምታደርጉት ግንኙነት በኛ በኩል እንዲሆን ተፈራርማችኋል እንዳሉት ሁሉ ይኸኛውም ውል ቢፈረም ኢትዮጵያ ምርቶቿን ለዓለም ገበያ የምታቀርበው በዩጎዝላቪያ በኩል ነው የሚል ትርጉም የሚሰጥ ነበር" (ገጽ 271)፡፡ "ብራቮ" አምባሳደር ታደሰ!

አቶ ታደሰ ስለሶቪየት ዩኒየን ጉብኝታቸው የሰጠን አስተያየት ፖለቲካ ያልለወጠው ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያወጣበታል፤

ጎርባቾቭ በሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ለጉብኝት ሞስኮ ሄዶ ጎርባቾቭ እንደ ሶቭየት ዩንየን ሁሉ በኢትዮጵያም በየአቅጣጫው ለውጥ ስለማስፈለጉ ሰፊ ገለጻ ያደርጋል ወይም ትምህርት ይሰጣል፡፡ መንግሥቱ ሰውየው የሚለው ስላልጣመው አንገቱን ዞር አድርጎ፥ ይሄ ቀልባሽ ከላሽ ብሎ ያልጎመጉማል፡፡ ምንድነው የሚለው? ብሎ ጎርባቾቭ አማርኛ ተሚያውቀውን ተርጓሚው(ን) ሸራየቭን ይጠይቀዋል፡፡ ሸራየቭ በበኩሉ፥ አይ ምንም አይደለም፥ ወይም በቅጡ አልሰማሁም ብሎ ነገሩን አድበስብሶ እንደማለፍ ፍርጥርጥ አድርጎ ቀልባሽ በራቹ ይልዎታል አለው (ገጽ 255-6)፡፡

አስተርጓሚው እዚያ የተገኘው የተባለውን እንዲያስተረጉም፥ የተጠየቀውን እንዲመልስ ብቻ ሳይሆን፥ የእንግዶቹን አስተሳሰብ እንዲሰልል ጭምር ስለሆነ ያየውንና የሰማውን "ቱስ" (በአቶ ታደሰ አነጋገር) እንዲል ጭምር ነው፡፡ ሰላይ በስለላ ያገኘውን አይደብቅም፡፡ አቶ ታደሰ ስለዋሽንግተን ጉብኝቱ ዘገባም ተመሳሳይ ነገር ይታይበታል፤ እንዲህ ይላል፤

ከሰባት ዓመት በፊት ይመስለኛል ዋሽንግተን አካባቢ የሚኖሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን አዲስ አበባ እንዲሄድ የተሾመውን አዲስ የአሜሪካ አምባሳደር ቀጠሮ ጠይቀው ያነጋግሩታል፡፡ (ስ)ለኢትዮጵያ ታሪክ፥ የወያኔ ከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ አደገኛነትና ኢትዮጵያን ስለሚጠብቃት የመገነጣጠል ወይም መፈራረስ እጣ ልባቸው ውልቅ እስኪል ይገልጹ(ለ)ታል፡፡ . . . ሰውዬው በአንክሮ ከሰማቸው በኋላ እንዲህ ይላቸዋል፡፡ "አንድ ያልተረዳችሁት ጉዳይ አለ፤ እኔ እኮ የአሜሪካ አምባሳደር ነኝ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ወይም ጥቅም ጠባቂ አይደለሁም፤ እያንዳንዱን አገር የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለው

> በዜጎቹ ላይ ነው፤ እኔ ኢትዮጵያ ስሄድ እንድከታተል መንግሥቴ የሚልከኝ የአሜሪካ ጥቅም እንዳስጠብቅና በአሜሪካ ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት ወይም ጥቃት እንድከላከል ነው" አላቸው፡፡ ሰዎቻችን ጉድ አሉ (ገጽ 265)፡፡

ኢትዮጵያውያን አምባሳደሩን ማነጋገራቸው የሚገባኝና የምጠብቀው ነው፤ "ሰዎቻችን ጉድ" ማለታቸው ግን አይገባኝም፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ የአምባሳደር ታደሰ መልእክት በልቦናችን ማደር የሚገባው ነው፡፡ የኛ ጉዳይ የኛ ነው፡፡ አሜሪካኖቹንና ሌሎቹንም የምንላቸው "ጨቋኝ ገዢን ስንታገል ጨቋኙን ብትደግፉ ሕዝብ ትጎዳላችሁ እንጂ፥ ምንም ዓይነት ጥቅም አታገኙም" ነው፡፡

የደራሲው የአገሩ ልጅ አምሳ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ ባይቀደም ኖሮ ከኢሕአፓ ጋር ሆኖ መንግሥት ሊገለብጥ አስቦ ነበር፡፡ አቶ ታደሰ እዚህም ላይ የሚያከራክር ግምት አለው፤ "እነአለማየሁ እነመንግሥቱን አሸንፈው ስልጣን ቢይዙ ኖሮ የኢትዮጵያ ታሪክ ምን ይመስል ነበር? ለሚለው ጥያቄ መልሱን መናገር ባይቻልም በወታደር አገዛዝ ዴሞክራሲ ይሰፍን ነበረ ወይም የወታደሩ ክፍል ሥልጣኑን በፈቃደኝነት ለሲቪል ያስረክብ ነበር የሚል ካለ ተአማኒነት አይኖረውም" (ገጽ 151) ይላል፡፡ የዓለማየሁ ቡድን ሥልጣን ቢይዝ፥ ዴሞክራሲ ይሰፍን ነበረ ወይም ሥልጣኑን በፈቃደኝነት ለሲቪል ያስረክብ ነበር ማለቱ እንደሆነ ማርክሲስቶች መንግሥት በመገልበጥ የያዙትን ሥልጣን እንዲህ ባለ ጨዋነት ለሲቪል ያስረከቡበት አገር መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

ግን መንግሥቱን ለማስወገድ የሞከሩ ጀኔራሎች ሙከራቸው ስለከሸፈባቸው አዝነን ነበር፡፡ ዓላማቸው ከመንግሥቱ የባሰ ርቆ የሚሄድ መሆኑን ከውስጥ ዐዋቂዎች ያገኘው አቶ ታደሰ ገብረ ኪዳን "አድማቸው እንኳን ከሸፈ" ይለናል (ገጽ 313)፤ እንዲህ ከሆነ እንኳን ከሸፈ፡፡

የ1976 ዓ.ም. (1984 ዓ.እ.) ድርቅ የጎዳውን አካባቢ አይቶ ገጽ 328-320 ላይ የዘገበው የሚያሰቅቅ ታሪክ እኔ ስለ 1973 ዓ. እ. ድርቅ ከማውቀውና ከመዘገብኩት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው፡፡ ሰዉ የሚበላው ስላጣ ከብቱንና ቅርሱን በተገኘ ዋጋ ይጥለው ነበር፡፡ ታደሰ ያንን ሲያይ ከዚህ በታች ያለው የሚያስገርም ሐሳብ መጣለት፤

> ሰንበቴ፥ ሰሜን ሸዋ፥ ስንደርስ አንድ የጣልያን ተወላጅ የተራበው ሕዝብ የሚሸጠውን የብር ጌጣጌጥ ሲገዛ አየን፡፡ . . . ሰውዬው የሚገዛበት ዋጋ ጌጦቹ በገበያ ከሚያወጡት ዋጋ አንድ መቶኛ እንኳን እንደማይሆን ግልጽ ነበር፡፡ . . .
>
> አዲስ አበባ በተመለስን ማግስት ሚኒስትሩ ሻለቃ ግርማ ይልማ ቢሮ ሄጄ በተለይ በሰንበቴ ያየሁትን ነገርኩት፡፡ "የባህል ሚኒስቴር ጌጦቹን በተወሰነ ዋጋ ይግዛ፤ የሻጮቹን አድራሻ በቅጡ መዝግቦ ይያዝ፤ ክፉው ቀን ካለፈ በኋላ ሚኒስቴሩ የከፈለውን ገንዘብ ተቀብሎ ጌጦቹን ለባለቤቶቹ ይመልስ" የሚል ሐሳብ አቀረብኩለት፡፡ "ጥሩ ሐሳብ ነው፤ አስፈላጊውን አደርጋለሁ" ብሎ አሰናበተኝ፡፡ ጥቂት ወራት ቆይቼ ምን እንዳደረገ ጠየቅሁት፡፡ ወደ ሰንበቴ ሠራተኞቹን ልኮ ከሚሸጡት ጌጦች በያይነቱ ገዝተው እንደተመለሱና በናሙናነት ተመዝግበው እንደተያዙ ነገረኝ (ገጽ 333)፡፡

ድርጊቱ በፈርዖናውያን ዘመን ግብጽ ረኀብ ገብቶ ዮሴፍ እንዴት እንዳዳናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የሚነገረውን ታሪክ ያስታውሳል፡፡ ድርቅ ተፈጥሮ ያመጣው ችግር ነው፡፡ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ ታደሰ ያላነሣው ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ አለ፤ ደርግ ለሕዝብ ሥራ በመፍጠር ፋንታ፥ ድንገት ተነሥቶ፥ ገበሬ፥ ነጋዴ፥ ቤት አከራይ በመሆን የሕዝቡን ሥራ በመንጠቁ የብዙ ቤት እንጀራ ሲዘጋ፥ ሕዝቡ በዚህ በደርግ ሠራሽ ችግር ላይ ወድቆ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ጌጣ ጌጦቹን "በገበያ ከሚያወጡት ዋጋ" በታች ሸጧቸዋል፡፡

ወደመግቢያዬ ላይ ስለአባቶቻችን አርአያነት ስናገር "አርአያነታቸውን ለዘመኑ በጎ ገጽታ እንዲስማማ ያህል በጥቂቱ ካስተካከሉ በኋላ በብዛት እንዲያጥለቀልቁን እመኛለሁ፡፡ ምን

ማለቴ እንደሆነ በኋላ በአንድ ጥቅስ እገልጻለሁ" ብዬ ነበር፤ ቃሌን ለመጠበቅ፥ አቶ ታደሰ ሊያስገርመን የጻፈውን ተረት-መሰል እውነተኛ ታሪክ ልቅጻና ላስገርማችሁ፡፡ እንዲህ ይላል፤

> በወቅቱ የእንጀራ እናቴ እማማ ባዴቺ ሿጌ ነበረች፡፡ . . . አባባና ባዴቺ የሳንቃ ገብተው ሳለ የአባባ ወቢሳ አሎ ልጅ፥ እልፍነሽ፥ ውሃ ለመቅዳት በቤታችን ደጃፍ ስታልፍ ባዴቺ ታይና "ታያታለህ ገጎ? ይህች ልጅ እንዴት ታምራለች!" ትላቸዋለች፡፡ አባባ ያኔ ቢያንስ አምሳ ዓመት አያጡም፡፡ እልፍነሽ ግፋ ቢል ዐሥራ ስምንት ቢሆናት ነው፡፡ አባባ ልጅ መውለድ ይፈልጋሉ፡፡ ባዴቺ አልቋጥር አለች፡፡ ባዴቺ ሳታውቅ አባባ በምስጢር ሽማግሌ አባባ ወቢሳ ዘንድ ይልኩና እልፍነሽን ያስጠይቃሉ፡፡ ይሰጣሉ፡፡ ባዴቺ ብትፈርጥ፥ ብትቀጠቀጥ ያለቀለት ጉዳይ ሆነ፤ እያለቀሰች ቤቱን ጥላ ወጣች (ገጽ 57)፡፡

እንዲህ ያለውን ባህል እንዴት ነው የምንላቀቀው? የሚያስለቅቀንስ ማንው? ማጭበርበር፥ ብልጠት ነው፤ ሲሾሙ አለመብላት ሞኝነት ነው፤ ስንፎክር "ዘራፍ" እንላለን፡፡ በባህላች ዘርፎ መብላት ጉብዝና መሆኑ ነው፡፡ አርአያነታቸው ቅዱሱ መጽሐፍ በሚያስተምርበት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን እመኛለሁ፡፡

አምባሳደር ታደሰ በአምባሳደርነት ሥራው ምክንያት ከኢትዮጵያ ለመውጣትና የጥገኝነት ፈቃድ ለማግኘት እንደብዙዎቻችን አልተቸገረም፤ ለመቋቋም ግን ከፍ ያለ ችግር ደርሶበታል፡፡ ወያኔዎች ኢትዮጵያን መግዛት ሲጀምሩ፥ መጀመሪያ ያደረጉት አገር ወዳዱን የመንግሥት ሠራተኛ ማባረር እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ታደሰን ሲጠሩት፥ ስለሀገሩ ያለውን አስያየት እንደሚያውቁ ቀደም ብሎ ስለሚያውቀው ጥሪያቸውን አላከበረም፤ በቊጥጥሩ የነበረውን ገንዘብ እነሱ እንዲዘርፉት አስረክቧቸው ከኤምባሲው ወጣ፡፡ ይኸን ስል ገንዘቡን ስለማስረከቡ በግሌ የማውቀው ነገር ኖሮኝ ሳይሆን፥ ታደሰ የሚታመን ሰው ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡ ደግሞም ይህን ለማድረጉ "ከጉዳይ ፈጻሚው ደረሰኝ ተረክቤ ኤምባሲውን ለቅቄ እንድወጣ በተባልኩበት ቀን ጥዬ ወጣሁ" (ገጽ 407) ብሎ አይጽፍም፡፡ "ደረሰኙን አሳየን" ቢባል ያሳያል፡፡ ኤምባሲውን እንደለቀቀ ሰባት እራሱን ሆኖ ከዘመድ ዘንድ በደባልነት ተጠጋ!

በሞያው ሥራ ቢፈልግ፥ ማግኘት አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚከፍለው ከሲታ ደሞዝ በተቆጠበ ገንዘብ ቤት መከራየትና ብዙ አፍ መሙላት የማይታሰብ ነው፡፡ አገሩ ካናዳ ስለሆነ፥ ጦም አይታደርም፤ ግን በጎ አድራጎት ቢሮ ሄዶ (በደራሲው አነጋገር)፥ በዕፅ ከደነዘዘ፥ በመጠጥ ከተለከፈ፥ የሥራ ሐሞቱ ከፈሰሰ፥ ወንጀለኛ በመሆኑ ቀጣሪ ካጣ ጋር መኮልኮል ቀላል አይደለም፡፡ "(አውቶሞቢል አልነበረንም፡፡ ባለቤቴ) ዕፀገነት የሚታጠቡ ልብሶቻችንን በጀርባዋ ተሸክማ አጥባ ተመልሳለች፡፡ እስከዛሬ የሚገርመኝ ሰፈራችን ግርጌ ያለውን ዳገት በዚያ የነሐሴ ሙቀር እንዴት አድርጋ እንደወጣችው ነው" የሚለውን ሳነብ ሰውነቴን ሰቅጠጥ አለው፡፡ ጥገኝነት ያገኙት አባ ወራው ሕፃን ልጁን በአንቀልባ በደረቱ አዝሎ መሄድ ቅዱስ ባህል በሆነበት በካናዳ ስለሆነ፥ ዕፀገነት ይኸን ያደረገችው አባ ወራው ታደሰ ሳያይ መሆን አለበት፡፡

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፥ እንዲህ በችግር ላይ ሳሉ፥ አብራቸው የነበረች የወይዘሮ ዕፀገነት እኅት አረፈች፡፡ እዚያ ታሪክ ላይ ስደርስ እጄ መጽሐፉን መሸከም አቃተው፡፡ ችግሩን ለመቋቋም የቻለው በዕፀገነት ጠንካራ መንፈስ ነው፡፡

ከብዙ እንግልት በኋላ፥ እግዚአብሔር ረድቶት (ደራሲው በእግዚአብሔር ማመን አለማመኑ ግልጽ አይደለም) በ አይ ኤም ኤፍ (IMF= International Monetary Fund) በኩል የጥቂት ወራት የኮንትራት ሥራ አግኝቶ ወደላይቤርያ ሄደ፡፡ እዚያው ብዙ ዓመታት ቆይቶ ለሀገር እድገት ደንታ የሌላቸውን ባለሥልጣኖች በዚያ በተዋሐደው ገታራነቱ ተጋፍጦ ኤኮኖሚያቸውን አዳነላቸው፡፡ የኛይቱ ኢትዮጵያ ካላቸው ቀላውጣ ያስተማረቻቸው ልጆቿ የብዙ አገር ኢኮኖሚ እያቋቋሙ ነው፡፡ እውነት ይሁን ቀልድ ባላውቅም ስለዚህ ነገር የሰማሁትን ልናገር፤ በአንድ ታላቅ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስብሰባ ላይ የብዙ አፍሪካ አገሮችን

ወክለው የመጡት በአንድ ቋንቋ ሲነጋገሩ አንድ አውሮፓዊ ሰምቶ፥ "እናንተ ከየሀገሩ የመጣችሁ አፍሪካውያን ሁላችሁም የምትነጋገሩበት አንድ ቋንቋ እንዳላችሁ አላውቅም ነበር" አለ ይባላል:: ሰውዬው ሰዎቹ በባህል ሁሉም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውንና የሚነጋገሩትም በአማርኛ መሆኑን አላወቀም:: ለነገሩ ቋንቋው ባለብዙ ቋንቋ ለሆነችው ኢትዮጵያ ተመሳሳይ አገልግሎት ሲሰጥ የኖረና አሁንም በመስጠት ላይ ያለ ነው::

ታደሰ በአጋጣሚው ስለላይቤሪያ፥ በተለይም ስለዓሥር አለቃ ዶ እና ስለቻርልስ ቴይለር የግዛት ዘመን የጻፈው ታሪክ የሚያስርም ነው:: አገሪቷን ያቋቋሙት ከአሜሪካ የሄዱ ጥቁሮች በነባሩ ላይ ነግሠውበታል:: ከአሜሪካ ያመጡት ጌትነትና ንቀት እንጂ ለሀገሬው የሚጠቅም ዕውቀት አይደለም:: ለማንኛውም ነፃ ወጥተው "ከአሜሪካ የተመለሱትንም" ሆነ አሁን ያሉትን ዝርያዎቻቸውን "መጤ ጥቁር ባሮች" (ገጽ 457) ማለት ግን ስሕተት ነው:: ባርነት ጭቆና በሰው ልጅ ላይ ያበጣቅ ወንጀል ነው እንጂ የዘር አይደለም፤ አንድ ሰው ነፃ ከወጣ በኋላ እንደማንም እንዳልተገዛ ሰው ነፃ ነው:: ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ ካወጣቸው ወዲህ ማንም "ባሮች" አይላቸውም::

ባርነት የዘር አለመሆኑን የሚያሳየው ቃሉ ጭምር ነው:: ራሳቸውን ችለው ለመቆም የማይችሉ ቃላት "ጥገኛ ቃላት" ይባላሉ:: "ባርያ" ከነሱ አንዱ ነው፤ ሌሎቹ "ጆሮ"፥ "አፍንጫ"፥ "ዜጋ"፥ ወዘተ ናቸው:: ለምሳሌ፥ "ጆሮዬን፥ ዓይኔን፥ አፍንጫዬን አሞኛል" ይባላል እንጂ፥ "ጆሮ፥ ዓይን፥ አፍንጫ አሞታል" አይባልም:: "ዜጋ" እና "ባርያ"ም እንደዚሁ ናቸው፤ ለምሳሌ፥ "እገሌ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው"፤ "እገሌ የእገሌ ባርያ ነው" ይባላል እንጂ፥ በደፈናው "እገሌ ዜጋ ነው"፤ "እገሌ ባርያ ነው" አይባልም::  የማን ዜጋ? የማን ባርያ? ሲባል መልስ ሊኖር ይገባል::

አቶ ታደሰ ሕዝባዊ ስሆነ ይመስለኛል፥ ቋንቋው (አማርኛው) ሕዝባዊ ነው፤ "ወይዘሮ ውሺት"፥ "አያ አማርኛ"፥ "አቶ ሁሉን በሆዴ"፥ "ተስፍሽ"፥ "መንጌ"፥ "ጂኒጃንካ"፥ "እንትን አለቀ ቢሉት እንትን ቀለለ"፥ "እገሌ ቱስ አለልኝ" የሚል አነጋገር ከልብ ወለድ ውጭ በሆነ ስነ ጽሑፍ ውስጥም ቦታ አግኝተዋል፤ እኛም (በጸሐፊው አገላለጽ) "መቸስ ማል ጎደኒ" ብለን መቀበል ይኖርብን ይሆናል::  ግን "ሰይ ብንል ብናከረባብት" (ገጽ 462) ማለት ምን ማለት ነው? ሁለተኛም፥ የአንድ ደራሲ ስም በራሱ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ሲጠራ ሳይ ለመጀመሪያ ጊዜ *ብዙ አየሁ የሕይወቴ ታሪክና ትዝታ* ውስጥ ነው:: መጽሐፉን ትልቅ ያደረገው ደራሲው እንደጥንት የሃይማኖትና የግብረ ገብ መምህራን ያደርጉት እንደነበረው፥ አንድ ድርጊት ባጭሩ ተርኮ፥ ከታሪኩ የሚገኘውን ትምህርት ስለሚሰጥ ነው:: ዋና ዋናዎቹ ትምህርቶች ተሰብስበው ገጽ 472-4 ተጽፈዋል:: እዚያ፥ "አታዳላ" እና "ፍትህ አታዛባ" የተለያዩ ምክር ሆነው ተመዝግበዋል:: የገባኝ የዓርባ ቀን ዕድል እንደማይለወጥ ነበር፤ ታደሰ "ዕድልና ሰው ከጊዜ ጋር ተለዋዋጭ መሆናቸውን አትርሳ" አለኝ::

*ብዙ አየሁ ብዙ* ተጠቅሰው የማያልቁ፥ ግን ሊጠቀሱ የሚገባቸው መጠናቸው ታናናሽ፥ ቁም ነገራቸው ታላላቅ አንቀጾች ይዟል:: መጽሐፉ የግል ታሪክ ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንዱ ክፍል ስለሆነ፥ በዚች አጭር ድርሰት የጠቃቀስኩለት ታሪክ የሚወዱ ኢትዮጵያውያን ባያነቡት የሚቀርባቸው ምን እንደሆነ በዓይናቸው እንዲያዩት ያህል ነው:: ኢትዮጵያዊ መንግሥት ሲቋቋም፥ ምናልባት ተማሪዎች በመምህር መሪነት እንዲያነቡት የሚደረግ መጽሐፍ ነው:: እንደገና የሚታተም ከሆነ፥ አጠራረዙ ጠንከር እንዲል ሊታሰብበት ይገባል::